# የጋማ ከብቶች ጥል

ከጋሜ ጎሹ (ኖርዌይ)
እና
ከዙዋይ ረዚን (ጀኔቫ)

አህያና አሣማ በቅሎና አጋሰስ
ድኩላና ፍዬል መጋጃ ፈረስ
በወሬ ተጣልተው ጠፉ መላቅጡ
በጎሣ ጥሩምባ መሪ እየመረጡ
ይዋጣልን ብለው ከጃንሜዳ ወጡ
ባሕርን አቋርጠው እየተሯሯጡ
ጅብ ተኩላና እባብ ሳይጠሩ መጡ
ለአሸናፊ ወገን ዋንጫ ብር ሊሰጡ
አቅም ያልፈቀደላቸው ድመትና ዶሮ
ይኼን ጉድ ያዩ ነበር ተገን ይዘው ጓሮ
ከብት አብዶ ሲራገጥ አናይም እያሉ
ሰዎች ጫካ ገቡ ከተማ እየጠሉ
ትንኝና ቢምቢ ባንዴ እየበረሩ
የእንስሶቹን ቁርሾ ደህና እያሳመሩ
ስለማይቀረው ጥል ላገር ተናገሩ
ከዚያ ብዙ ሳይቆይ ወጣ ድብልቅልቁ
በቀንድ በርግጫ እንስሶች ተዋቁ
ግንጥልጥል እስኪሉ እየተናነቁ
አይን እስኪጠፉ እስኪወጣ ፈርሱ
ሊገነጣጠሉ እንስሶች ተነሱ
የጥሉ እሳት ጠፍቶ እንዳይቀዘቅዝ
ማራገብ አበዙ ቢምቢና ነቀዝ
“መብትህ ነው መዋደቅ በርታ ጂሎ” እያሉ
ከዝርግፍ ሽንፍላ ዝምቦች ብዙ በሉ
ልብ የከዳው ጊዜ ፍየል እየባባ
አገሩ ጠፍቶበት ክልል ወህኒ ገባ
ከግጦሽ ላይ ውሎ ለጥሉ ዘግይቶ
የበጎች ሠራዊት መጣ ተጎትቶ
ከአብሮ አደጎቹ ፈረስና በቅሎ
ምን ብዬ ልጣላ ምን ቂም አለኝ ብሎ
ማመንታቱን ሲያዩ ብልሃቱ ጠፍቶት
“ለካ እውነትም በግነህ በለው እንጂ” አሉት
ስብከቱን ሲሰማው በጭንቅ ልቡራደ
ሳይቸግረው በጉ መለስ ብሎ አበደ
ለጎሣዬ ብሎ ሊጣላ ከዘሩ
ተሰልፎ ቆመ በግም በግምባሩ

የነገድ በሽታ እስካልተጠረገ
መተዳደሪያውን ሕዝብ ካልደነገገ
ወያኔ ወይኔ ይበል እየበረገገ
ደግሞም መክፈሉ አይቀር ከባዱን ወንጀል
በጎሣ አሰልፎ ሕዝብን ማጋደል
አገር ከሚናከስ አደገኛ ትል
ወጌሻው ባሩድ ነው የሚገላግል!

አታሎ ለመግዛት በመከፋፈል
ከርቸሌ ቢያጣብብ በደም ቢበከል
ክላሺኑን ቢያጎርስ መትረዬስ ቢያንጣጣ
በአገሩ መጥፋት የአገር ሕዝብ ሲቆጣ
አያድርስ ይሉታል የወያኔን ዕጣ!

ለአገር ክህደት ወንጀል የለውም ምሕረት
ሱባኤ ቢገቡ ባፅም በፀሎት
ሕሊናን ቢሰው እንደበረከት
ለማንም አይሆንም ርካሽ ታምራት!
በፍርሃት ከሚኖር እየተወጠረ
የአልባኒያ ጋሪውን በጂብ ከቀየረ
በጥምዘዛ መንዳት ዱር እንደተማረ
በኋላ ማርሽ መለስ ቅላልነው ነበረ!
መንደር ውስጥ ብትውል ስቧት ጥምብ ሽታ
ለምድ ለብሳ ብትዞር ተኩላ ጥዋት ማታ
ስንቋ ዱላ ይሆናል የነቁባት ለታ
የማይመች ነው በቀን ማታለል
ኮከብ አልቀናም ሲል ለስንኩል ዕድል
ሄዋን ስቅስቅ አለች ለኢትዮጵያ አዝና
ንዴቷ ገንፍሎ በረታባትና
ጥፍሯን አሣድጋ የነብር ወይዘሮ
ጃርትን ልታባርር ቆርጣለች ዘንድሮ!

ኦሆሆ አሃሃ እያለ ጨፈረ
ሕሊናውን ሳተ በቦርዴ ሠከረ
ዴዴሣ ይውሰደኝ ሲል ተግደረደረ
ድርሳነ ወያኔን በላቲን ዘመረ

ኦ ሆሆ ደዳዴድ
ኢሕሒሃሃ ኦኦዴድ!

------------------------------------------------

TPLF and EPLF cannot be reformed, like apartheid, they should be abolished!